**ቀን ________________ዓ.ም**

**መዝ/ቁ_______________**

# <u>የውክልና ሥልጣን ማስረጃ</u>

**ወካይ ፦ ________________________________ፓ.ቁ EP______________ ዜግነት ኢትዮጵያዊ/ት**

**አድራሻ፦ ሣዑዲ አረቢያ ከተማ ጅዳ ስ.ቁ ቁ____________________**

**ተወካይ፦ __________________________ ዜግነት ኢትዮጵያዊ/ት መታ/ቁ____________**

**አድራሻ፦ ከተማ___________ ክፍለ ከተማ_____________ ወረዳ ______ ስልክ ቁ___________________**

እኔ ወካይ ከላይ ለተጠቀሰው ተወካይ የሚከተለውን የውክልና ሥልጣን ሰጥቻቸዋለሁ፡፡

ተወካይ እንደ እኔ በመሆን በኢትዮጵያ በየትኛውም ክልል በስሜ ማንኛውንም አይነት ንብረት ህግ በሚፈቅደው መልኩ እንዲገዙልኝ፤ በስሜ እንዲያስመዘግቡ፤ ወደስሜ እንዲያዘዋውሩ ሊዝ ቦታ እንዲዋዋሉ መፈረም እንዲችሉ ተመዝግቦ የሚገኘውንም ሆነ ወይም ወደፊት በስሜ የሚመዘገበውን የሚንቀሳቀስ እና የማይንቀሳቀስ ንብረት የአክሲዮን ማህበር ወይም የጋራ የመኖሪያ ቤት ወይም የኮንዶሚኒየም የመኖሪያ ቤት የከተማም ሆነ የገጠር የመኖሪያ ቤት ወይም የማህበር እና የአክሲዮን የሥራ እና የመኖሪያ ቤት ወይም የገጠር የእርሻ ቦታ የሊዝ ቦታ ወይም የንግድ ቤት፤ መኪናና፤ ሱቆች ፋብሪካ ፤ወፍጮ ወዘተ ሀብትና ንብረቶችን ወደስሜ እንዲያዘዋውሩ በስሜ እንዲያስመዘግቡ እንዲገዙ፤ እንዲቆጣጠሩ፤ እንዲገነቡ፤ በአደራ እንዲጠብቁ፤ ስጦታ እንዲቀበሉልኝ፤ ቁልፍ አነዲረከቡ ፤ እንዲያከራዩ ፤እንዲያለሙ ሰራተኞች እንዲያስተዳድሩ ካርታ እና ፕላን እንዲቀበሉ በስሜ በየትኛውም ክልል በአክስዮን ወይም በማህበር በመደራጀት ለመኖሪያም ሆነ ለንግድ ድርጅት መስሪያ ወይም ለእርሻ እና ለእርባታ የሚሆን ቦታ እንዲረከቡ፣ የግንባታ ፈቃድ በማውጣት ሙያተኛ ቀጥረው ግንባታ እንዲያካሂዱ፣ መረጃ እንዲቀበሉ፣በስሜ የተመዘገበውን የከተማ የስራ እና የመኖሪያ ቤት ሆነ የገጠር የእርሻ መሬት መንግስት ለህዝባዊ መንግስታዊና ለሀገራዊ ልማት ስራ ለባቡር ወይም ለልዩ ልዩ ግልጋሎቶች ቢፈልገው ከመንግስት ተለዋጭ መሬት እንዲቀበሉ ከኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ወይም ከሌሎች መንግስታዊ ወይም የግል ህጋዊ ባንኮች ገንዘብ ገቢ እንዲያደርጉ እንዲከታተሉ ከኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ቼክ እንዲቀበሉ፣ የአክሲዮን ወይም የማህበር ስብሰባዎች ላይ እንዲሳተፉ፣ ድጋፍ እንዲሰጡ፣ እንዲቃወሙ፣ ድምፅ እንዲሰጡ፣መተዳደሪያ ደንብ ላይ እንዲፈርሙ ቃለ ጉባኤ ላይ እንዲፈርሙ መመስረቻ ፅሁፍ ላይ እንዲፈርሙ በስሜ የተመዘገበውን የአባልነት የማህበርና አክሲዮን እንዲቆጣጠሩ፣ በስሜ የንግድ ፈቃድ ማደስ፣ መሰረዝ ፣ በጉምሩክ ባለስልጣን ያሉኝን ጉዳዮች እንዲፈፅሙ፣ የቀበሌ መታወቂያ እና መንጃ ፈቃድ እንዲያድሱ ኢንሹራንስ እንዲገቡ በኢትዮጵያ ውሃና ፍሳሽ ባለስልጣን፣በኢትዮጵያ መብራት ሃይል መ/ቤት፣ በኢትዮጵያ ቴሌኮሙኒኬሽን ኮርፖሬሽን መ/ቤት ውስጥ የሚኖሩኝን ጉዳዮች እንዲፈፅሙና እንዲያስፈፅሙ እንዲሁም ከማንኛውም የመንግስት መ/ቤቶቹ ጋር መልካም የሆኑ ግንኙነቶችን በመፍጠር ለመንግስት የሚከፈሉ ክፍያዎችን ግብር እና ታክስ እንዲከፍሉ፣ከእዳ ነፃ መሆኔን እንዲያረጋግጡ፣ በምከስበትና በምከሰስበት ወቅት እንዲሁም በውርስ በግዥ በስጦታ ወይም በተለያዩ ጉዳዮች በንብረቴ ላይ ክርክር በሚነሳበት ወቅት እንደ እኔ በመሆን እንዲከራከሩ፣መልስ እንዲሰጡ፣ይግባኝ እንዲጠይቁ ቃለመሃላ እንዲፈፅሙ፣በስሜ በተዘጋጀ ሰነድ ላይ እንዲፈርሙ፣ከላይ በዘረዘርኩት መሰረት የእኔን የወካዩን ጉዳይ በተመለከተ በመንግስትና አስተዳደር መ/ቤቶች፣ፍ/ቤት፣

ማዘጋጃ ቤት፣ቀበሌና ሌሎች የሚመለከታቸው አካላት ፊት በማቅረብ እንደእኔ በመሆን ጉዳይ እንዲፈፅሙና እንዲያስፈፅሙ ይህንን የውክልና ሥልጣን በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 2199 እና 2203፣2204 መሠረት የሠጠኋቸው መሆኔን በፊርማዬ አረጋግጣለሁ፡፡

**የወካይ ስም እና ፊርማ**

________________________________